# የአማራ ክልል



# ባለፉት15 ዓመታት (1985-2001) በክልሉ የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ የተከናወኑ ዋና ዋና ሥራዎች (መስከረም 2002 ዓ.ም)

## 1.የግብርናና ገጠርልማት ስራዎች ዋና ዋና አፈጻጸሞች

ባለፉት ሁለት የመርሃ ግብር አመታት (ከ1987-1992 እና ከ1993-2001)የነበረው ሁኔታ

- ከፍተኛ የግብርና ምርት ጭማሪ በተከታታይ ተመዝግቧል፡፡
- በምግብ ፍላጎትና አቅርቦት መካከል የነበረው ሰፊ ክፍተት እየጠበበ መጥቷል፡፡

### 1.1. የሰብል ምርት

አመታዊ የሰብል ምርት በያመቱ እየጨመረ ነው፡፡
ምርት ለስድስተኛ ጊዜ በተከታታይ ዕድገት አሳይቷል፡፡
የሰብል ምርት እድገት በተከታታይ በ15%፣
ምርታማነቱም ከ14 ኩንታል በሄክታር ወደ 17 ኩንታል በሄክታር ከፍ ብሏል፡፡
የመቶ ሺዎች አ/አደሮች ኑሮም በከፍተኛ ደረጃ ተለውጧል፡፡

የሰብል ምርት አመታዊ እድገት

| ተቁ | ዝርዝር ሥራ | 1986/87 | 2000/001 |
|---|---|---|---|
| 1 | የለማ መሬት ስፋት በሄክታር | | |
| | መኸር | 2,608,320 | 4,05,1963 |
| | በልግ | 172,000 | 166,000 |
| | መስኖ | 44,366 | 347,725 |
| 2 | የተገኘ ምርት መጠን በኩንታል | | |
| | መኸር | 23,846,130 | 60,614,094 |
| | በልግ | 507,300 | 1,058,103 |
| | መስኖ | 1,572,632 | 38,001,507 |

በ2001 ከ63 ሺህ ሄክታር በላይ ኮትቻ አፈር አጠንፍፎ ማልማት ተችሏል፡፡
በዚህም ምክንያት ላለፉት በርካታ ዓመታት ከምርት ውጭ ሆነው የቆዩና ቢያመርቱም ምርታማነታቸው በእጅጉ አሽቆልቁሎ የቆዩ መሬቶች ላይ ምርትን ከ 3 እና ከዚያ በላይ እጥፍ ማሳደግ የሚያስችል ሁኔታ ተፈጥሮአል፡፡
አሲዳማ አፈርን ማልማት በ1,224 ሄ/ር መሬት ላይ ተከናውኗል፡፡

# የመስኖ ልማት

- በመስኖ ሊለማ የሚችለውን መሬት 1986/87 ከ 60 ሺ. ወደ 347ሺ. ሄ/ር (በ57%) ማሳደግ ተችሏል::
- በምርት ከ1.6 ሚሊዮን ኩንታል ወደ 38 ሚሊዮን ኩንታል፤
- በምርታማነት ከ43 ኩንታል በሄክታር ወደ 60 ኩንታል በአማካይ ከፍ ሊል ችሏል::

የሽንኩርት ልማት በመስኖ (ፎገራ)

